የኢትዮጵያ ክፍለሀገራት ሕብረት Union of Ethiopian Provinces
www.ethiopianhibret.com ethiopianhibret@gmail.com

ጃኑዋሪ 4፣ 2018

*እናት አባት ቢሞት ባገር ይለቀሳል፣*
*ሀገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል?*

ኢትዮጵያሕብረትአስቸኳይጥሪ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት የበርካታ እምነቶች ተከታይ፣የብዙ ባህሎች ባለቤት፣የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ የሆነ ሕዝብ ተስማምቶና ተዋልዶ በሰላም የኖረባት አገር መሆኗን እንኳንስ ወዳጅ ጠላቷም የማይክደው ሃቅ ነው።ይህም ብቻ አይደለም፤ ከሁሉ ቀድማ የነጻነትና የብልጽግና ባለቤት የነበረች ታላቅ ሃገር፣ቅኝ ገዢዎችን አሳፍራ የመለሰችና ለሌሎቹም የአርነት ትግል ምልክትና አጋር ሆና ለነጻነታቸው ያበቃች ሀገር ሆና ሳለ፣ያች ታላቅ ሀገር አሁን በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ዓለም ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ላይ መድረሱ ቀርቶ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት ወደ ነበረችበት ዘመነ መሳፍንት ተመልሳ ልጆቿ በጎሳ ተከፋፍለው የሚተላለቁባት ሀገር ሆናለች።

የባዕዳን ጉዳይ ፈጻሚ የሆነው የወያኔ ማፊያ ቡድን፣ ኢትዮጵያውያንን ቅኝ ገዢዎችና ተገዥዎች አድርጎ በመከፋፈል ከባዕዳን የስለላ ድርጅቶች ጋር በመመሳጠር በአስተዳደር የተከሰቱ ችግሮችን የዘር አስመስሎ በማባባስ እርስ በርስ እንዲፋጁና አንድ የነበረች አገር እንድትከፋፈል አድርጓል።ወያኔ ከወዳጁ ሻእብያ ጋር ኢትዮጵያን በመዝረፉ የጥቅም ግጭት ምክንያት ባስነሱት ጦርነት ከመቶ ሺህ በላይ ህይወት ጠፍቷል፤ ብዙ ሺህ አካለስንኩላን ሆነዋል፣ ከመቶ ሺህ በላይ ዜጎች በሰላም ለዘመናት ከኖሩበት ኢትዮጵያ ሀገራቸው ንብረትና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ተባረዋል፣ በጦርነት ቀጠና አካባቢ የሚኖሩ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ወገኖቻችን እንዲፈናቀሉ አድርጓል።

ይህ ቡድን በቁጥር አነስተኛ ሆኖ ሳለ የአገሪቱን የኤኮኖሚ፣የፖለቲካ፣የመከላከያና የደህንነት ተቋሞች በመዳፉ ስር አስገብቶ በመያዙና የአገሪቱን የተፈጥሮ አንጡራ ሃብትና ለም መሬት ለባዕዳን በመቸብቸብ እንዲሁም በውጭ አገር ካሉት አጋሮቹ "በጸረሽብርተኛነት" ጭንብል ሆኖም ግን የራሱን ሕዝብ በማሸበር በሚያገኘው ከፍተኛ ሁለገብ የድጋፍ ተፋሰስ እብሪተኛና የሕዝቡን ጥያቄ ላለመስማት ጆሮውን እንዲደፍን አድርጎታል።በሚጠቀምበት የለያይተህ ግዛ መመሪያው ሕዝቡን እርስ በርሱ እያጋጨ እንደካርታ ቁማር ጨዋታ እየቀያየረ አንዱን በማስጠጋት ሌላውን በማራቅ፣አንዱን በዳይ ሌላውን ተበዳይ አድርጎ በመለያየት ለ27 ዓመታት መግዛት ችሏል።

በቅርቡ ግን ሁኔታዎች እየተቀየሩ መጥተዋል። ሲጠቀምበት የኖረው የከፋፍለህ ግዛው ስልቱ እየተሟጠጠና እየተጋለጠ ቅራኔው ከውስጡም እየተነሳበት፤ በስልጣኑ ላይ ለመቆዬት የሞት የሽረት ትግል እያደረገ ነው። ወያኔ በተለመደው መርዘኛ ሴራ "ኦሮሞና አማራ እሳትና ጭድ ናቸው"በሚል ሴራ ተላላኪዎችን አሰልጥኖ ሰላሌ እና በኢሊባቦር ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት የሸረበውን ሴራ በማጋለጥ የአማራና የኦሮሞ ወጣቶች ወንጀለኞቹን እጅ ተፍንጅ በመያዝ ለህዝብ በአደባባይ በማጋለጥ የንጹህ ወገኖቻችን ደም ከመፍሰስና ንብረት ከመውደም በማዳን ታሪካዊ ጀግንነት ፈጽመዋል። እነዚህ ወጣት የኦሮሞና የአማራ ልጆች ደማችን አንድ ነው፣ ሰላምና አንድነት እንጂ የርስ በርስ ግጭት አንፈልግም በማለታቸው ወያኔ አኩርፏል። እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚያበሩትን የተስፋ ችቦ ለማጥፋት ወያኔ ወጥመድ እየሸረበ ነው። ይህ የተጀመረው የወጣቶች ሕብረት ለፍሬ እንዲበቃ የወያኔን ደባና ተንኮል ተባብሮ ማክሸፍ፤ የወቅቱ አንገብጋቤ ጥያቄ ሆኗል።

ዛሬ በኢትዮጵያ ወጣቶች የተቀጣጠለው የለውጥ ማዕበል የወያኔን የፓርላማ በር እያንኳኳ መጥቷል። ለ17 ዓመት አቤት! ወዴት! እያለ፣ ወያኔን በታማኝነት ሲያገለግለው የኖረው ፓርላማ የሚባል የጎሰኞች በረት ወያኔ በሚያሳየው ጥጋብ እየተቦረቦረ መምጣቱ ተሰምቷል። የወያኔ ማፍያ ቡድን፣ በአምሳሉ የፈጠራቸው የብአዴንና ኦህዴድን ባለስልጣናት በሎሌነት ሲያስፈልግም በጥፊ እየቀጣ ሲገዛቸው የነበሩ ተላላኪዎቹ ፊታቸውን ወደ ህዝባቸው በማዞራቸው ጥርስ

የነከሰባቸው ቢሆንም እንደወትሮ ሊያንበረክካቸው ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች ተከስተዋል። ምናልባትም፣ ወያኔ እነዚህን ወጣት ባለስልጣናት እቀጣለሁ ብሎ ዱላ ቢያነሳ፤ የራሱን መቃብር መቆፈር ስለሚሆንበት የጠራው ስብሰባ እንደተለመደው፣ አገልጋዮቹን የመገላመጥ፣ በጋዜጠኛ ጋጋታ የማወናበድ፣ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መዝሙር ማደንቆር ሳይኖር ተዝረክርኮ ተበትኗል።

ይህ በመላው ሀገሪቱ የተቀጣጠለው ህዝባዊ ትግል በአሸባሪው የወያኔ ጎራ ፍርሃትና ሽብር አንግሷል። በቅርቡ በቋሚ ኮሚቴ ስም ያወጣው ዝርክርክ መግለጫ፣ ዘረኛው ቡድን ሊወጣ ከማይችልበት በመንታ ቀውስ ተዘፍቆ በሞት ሽረት መፍጨርጨር ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል። በአንድ በኩል የተነሳው ህዝባዊ ማዕበል በመላ ሀገሪቱ መቀጣጠሉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከውስጥ የተነሳበትን ቀውስ እንደወትሮው በዛቻና በጥፊ ሊገቱት ባለመቻላቸው እርስ በእርስ የሚቃረኑ መግለጫዎችን በማዥጎድጎድ ላይ ይገኛል። ይህ የወያኔ የመግለጫዎች ጋጋት ሀገር ለማዳን ነው ወይስ ወያኔን ለማዳን ብሎ መጠየቅ አስተዋይነት ነው። ቡድኑ የሕዝቡን ጥያቄ ለማንጸባረቅ የሞከሩትን የራሱን አጋር ድርጅቶችና መሪዎቻቸውን በክህደት ወንጅሎ ያስፈራራል። መለስ ብሎ ደግሞ “ካሮትና ዱላ” በመያዝ አዳዲስ ሆዳሞችን ለመመልመልና ሀገር ወዳዶችን ለመጥለፍ ወጥመዶች እያዘጋጀ መሆኑ ይታያል።

ስለሆነም፣ሀገር ወዳድ ሀይሎች ከእባብ እንቁላ ልእርግብ እንደማይፈለፈል ሁሉ ከወያኔ መራሹ ቡድን በጎ ነገር እንደማይመጣ ተገንዝበው ለዘላቂ ድል በህብረት መነሳት ይኖርባቸዋል።በጸረ ኢትዮጵያዊነት የተሳከረው የወያኔ ማፊያ ቡድን፣ኢትዮጵያዊነትን የሚያራምዱትን ወጣቶች ከመብላት ወደኋላ አይልምና ወደ ሕዝቡ እያደሉ የመጡት ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ለአደጋ እንዳይጋለጡ ማድረግ የሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ ግዴታ ሲሆን ይገባል።እነሱም ሕዝቡ ከጎናቸው መቆሙን ተገንዝበው ከአቋማቸው እንዳያፈገፍጉ የኢትዮጵያ ሕብረት በአክብሮት ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ ሕብረት አገራችን ያለችበትን ሁኔታ በማጤን የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል፤

1. የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ! ሕዝብ ጠንክሮ ከታገለ በመጨረሻ ላይ የድሉ ባለቤት መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ 97 የተጎናጸፈውን ታሪካዊ ድል በጦር መሳሪያ የነጠቀው የወያኔ አፋኝ ቡድን ለአለፉት 10 ዓመታት ራሱን ወደ ባሰ ቀውስ ከተተ እንጅ የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል አላዳከመውም። በመሆኑም፤ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ ትግል ለማዳከም የሚቆፍረው ጉድጓድ የራሱ መቃብር ይሆናል እንጅ የህዝቡ ትግል እንደማይቆም ተረድቶ ለህዝብ ጥያቄ መልስ መስጠት አለበት እንላለን። የፖለቲካ እስረኞች መፈታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያነሳቸውና ዋና ዋና ጥያቄው አንዱ ስለሆነ፣ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔ እንዲፈቱና ለደረሰባቸው የጤና፣ የቤተሰብ መፈናቀልና ሌሎችም ችግሮች መቋቋሚያ ካሳ እንዲከፈላቸው፣ እንዲሁም ማናቸውም ዓይነት ገደብ ሳይደረግባቸው በሀራቸው የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት የመሳተፍ መብታቸው እንዲከበርላቸው፤አፋኝና አሸባሪ የሆኑት አዋጆችም እንዲሰረዙ እንጠይቃለን።
2. የጦር ሀይሎች ሆይ! ፣ ወያኔ ለአለፉት 27 ዓመታት የጦር ሃይሎችና የደህንነት ቁልፍ ቦታዎችን በራሱ ብቻ በመቆጣጠር የአማራውንና የኦሮሞን የጦር መኮንኖች ተከታዮች አድርጎ መቆየቱ ሚስጥር አይደለም።ይህ ሁሉ በደል ሲፈጸም ሥርዓቱን አፋጥጠው የሚጠይቁት የአማራ እናየኦሮሞ ወጣቶች እንጅ ጄነራሎች አይደሉም።ይህ ሁሉ ፍርሀት ለምንድን ነው?ወያኔ በአማራና በኦሮሞ ጄነራሎች ላይ የሚያሳየው ንቀት ለአማራ ወይም ለኦሮሞ ሕዝብ ያለውን ጥላቻ የሚያሳይ ሲሆን፣በተለይም ደግሞ መሣሪያ ይዞ በሚታገለው የጦር ሃይል ላይ ያለውን ከፍተኛ ንቀት ነው።70% የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚወክሉትን የአማራና ኦሮሞ ማህበረሰቦች የምታሰድቡት እናንተ ናችሁ፤ የወያኔ ተላላኪዎች ሆናችሁ ወገናችሁ መጤ እየተባለ ሲገደል፣ ሲፈናቀልና ሲታሰርና ሲያለቅስ እናንተ ከወያኔ ጋር ትዘፍናላችሁ። የበታች ሹሞች የሆኑ የወያኔ አባሎች የሚያዛችሁ መሆኑን ወጣቱ ትውልድ ተገንዝቧል፣ ከታላቅ ማህበረሰብ ተፈጥራችሁ ተላላኪዎች በመሆናችሁ ህብረተሰቡ አዝኖባችኋል።እናንተንም በሰላም አስከባሪ ስም የጦር ሜዳ ሸቀጥ አድርጎ እየነገደባችሁ መሆኑን ልትገነዘቡት ይገባል።ይህ ማፊያ ቡድን፣ እናንተን ተገን አድርጎ ሕዝቡን እርስ በርሱ ለማጋጨት የሸረበውን ሴራ በማጋለጥ በእናት አገራችን ላይ ያንዣበበውን አደጋ በማክሸፍ ዛሬውኑ ከወገናችሁ ጎን እንድትሰለፉ ጥሪ እናደርጋለን፤
3. የእምነት አባቶች ሆይ፣በመጽሃፍ ቅዱስና በቅዱስ ቁርአን ቅድስት እየተባለች የተወደሰች ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ በእናንተ ጊዜ የተጫነባት ሥርዓት ግን ለሕዝብና ለእምነት ደንታና ክብር የሌለው በመሆኑ ሀገራችን አደጋ ላይ ወድቃለች። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ በጠላትነት ሲፈረጅ፣የሙስሊም ሃይማኖት በሰርጎ ገቦች ሲደፈርና ለመብታቸው የቆሙት ሲገደሉና ሲታሰሩ በዝምታ ማየት ከምን የመጣ ነው?በአምላክ አምሳል የተፈጠረው የሰው ልጅ፣ በግፍ ሲገደል፣ሲፈናቀል፣

ከግፈኞች ጋር ማበራችሁ ለምን ይሆን?ለምን ብላችሁ የመጠየቅና የማውገዝ ድፍረቱን ምን ነሳችሁ?ፍርሃት?ጥቅም ወይስ ስጋዊ ድሎት?አሁንም አልመሸም የሚጠበቅባችሁን ታሪካው ድርሻችሁን እንድትወጡ አደራ እንላለን፤

4. ወጣቱ ትውልድ ሆይ!ዛሬ በሀገራችን 65% ህዝቧ ወጣት ነው። የወያኔ መሀይሞች በ21ኛው ክፍለዘመን፣ በዘር ፖለቲካ ተሳክረው ወጣቱን በገፍ በእስር ቤትና በስደት እንዲሰቃይ ያደርጉታል። ይህ ማፊያ ቡድን፣ ከራሱ ጋር በርካታ የህብረተሰቡን ክፍል ይዞ ሊጠፋ እየተፍጨረጨረ ስለሆነ፣ ሀገርህንና የወደፊት እድልህን ለመጠበቅ ጠንክረህ ታገል። የምታደርገውን ትግል ለመቀልበስ ወያኔ አንዳንድ ኮሌጆችን ለሆዳቸው ያደሩ ሰላዮችና ካድሬዎች መፈልፈያ ፋብሪካ እያደረጋቸው ነው። ስለሆነም፣ ከዚህ አደጋ ራስህ ጠብቅ። ዛሬም እንደ ጥንቱ ለአገራቸው አንድነትና ለወገናቸው ክብር እንደወደቁት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ለወገኖችህ ጠበቃ ሁንላቸው።  የሀገር ተስፋ፣ የሕዝብ ዓይን፣ጆሮና ልሳን መሆንህን አትርሳ። ስርዓቱ የሚረጨውን የጎሰኝነት መርዝ በመድፋት እጅ ለእጅ ተያይዘህ የምታካሂደው ትግልና የምትከፍለው መስዋእት በታሪክ ለሚያኮራው አገራዊ ድል ስለሆነ ቀጥልበት።የ21ኛው ክፍለዘመን ትውልድ ነህና አስተሳሰብህ የዘመነ፣ከአስራአምስተኛው ክፍለዘመን ከጎሳ አመለካከትና ፖለቲካ የጸዳና የራቀ ይሁን። ሀገርህና ወገንህ አለም ከደረሱበት የስልጣኔና የእድገት ደረጃ እንዲደርሱ በጽናት ታገል።

5. የከተማው ሰርቶ አደሮች ሆይ! ሰርታችሁ የሰላም ኑሮ ልትኖሩ የምትችሉት ሰላማዊ አገር ሲኖራችሁ ብቻ ነው። ወያኔ በመጨረሻው ሰዓት ላይ በጥቅም በመደለብ በርካታ ሰላዮችና ወንጀለኞችን በማሰማራት ህዝብን ከህዝብ ጋር በማጋጨት ላይ  ስለሆነ ከዚህ አሮጌ ሥርዓት ጋር ሀገርንና ህዝብን በድሎ ለሚወድቅ ስርዓት ተባባሪ መሆን የኋላ የኋላ ለጸጸትና  ለሀፍረት ስለሚዳርግ ስለሀገርና የህዝብ ልዕልና ከጀግኖች ልጆቻችሁ ጎን ተሰልፋችሁ ታገሉ፤

6. የገጠሩ አርሶ አደሩ እና አርብቶ አደር ሆይ፣ለም መሬታችሁ ለውጭና ለውስጥ ቱጃሮች እየተሸጠ፣ እናንተ የእርሻና የግጦሽ መሬት ተቸግራችሁ፣ በወያኔ አጋዚ ጦር መጤ እየተባላችሁ ከትውልድ ቀያችሁ ትፈናቀላላችሁ።በማዳበሪያ ስም ትዘረፋላችሁ፣አሁን ደግሞ እርስ በርስ እንድትጨራረሱ እያደረጋችሁ ነው፤ይህን የወያኔ አጥፍቶ የመጥፋት ዓላማ ከውጥኑ  ከሌላው ወገናችሁ ጋር ተባብራችሁ አክሽፉት

7. በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራህ ሆይ! በሰላም ነግደህ እንዳታድር እንዲሁ በግብር ጫና ተስፋ ቆርጠህ  ለድህነትና ለስደት ተጋልጠሃል።ነግዶ ለማደር ያለህ መብትና ማንነትህ በሰው ልጅነትህና በዜግነትህ ሳይሆን የሚለካው በምትናገረው ቋንቋና ጎሳህ ነው።የአገርህ ገንዘብ ዋጋ ቢስ እየሆነ ከውጭ አስገብተህ ለመነገድ አልቻልክም።የንግድና የውጭ ምንዛሬው በአንድ ጎሳ ተወላጆች በሆኑት ቁጥጥር ስር ወድቆ  አንተና ቤተሰብህ የበይ ተመልካች ሆነሃል።ከሁሉም በላይ ያገርህ ህልውና አደጋ ላይ ወድቋል።ይህንን ሁሉ በደል እያደረሰብህ ያለውን ጨቋኝና አገር አጥፊ ቡድን ተባብረህ አስወግድ፤

8. ተቃዋሚ ያንድነት ሃይሎች ሆይ! የእናንተ በአገር አድኑ ትግል ተስማምቶ አለመሰለፍና ለሥልጣን በተናጠል የምታደርጉት እሩጫ የወያኔን ዕድሜ አርዝሞታል። ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። ሀገራችንን ከውድቀት፣ ህዝባችን ከበለጠ እልቂት ለመታደግ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት የሚፈለግበት ጊዜ ዛሬ ነው። ሀገራችንን እና ህዝባችንን ከመከራ የሚያድነው፣ ከወያኔ ጋር ስለሚቀጥለው ምርጫ መሸማገሉ ሳይሆን፣ ስለሚቀጥለው ትውልድ ህልውና የሚበጅ ሥርዓት መፍጠሩ ነው። የእናት ሀገራችን እጣ ፈንታ ወሳኞቹ ልጆቿ እንጂ የውጭ ባዕዳን ወይም ተላላኪዎቻቸው መሆን የለባቸውም። ስለሆነም፣ በሀገር ውስጥ ሆነ በውጭ የሚንቀሳቀሱ ተቀዋሚ ሀይሎች፣ ለወያኔ ጅቦች እድሜ የሆነውን “የበሬዎች ትግል” አቁመው፣ ዘር ተኮሩ ሥርዓት ተወግዶ፣ የእናት ኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ የህዝቧ ጽኑ አንድነትና እኩልነት፣ የህግ የበላይነት የሚከበርበት፣ ፍትህዓዊ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ለመፍጠር በአንድነት ቁሙ፤ትግላችሁ የወያኔን ሕገመንግስትና ስርዓቱን ለመለወጥ እንጂ ለመጠገን አይሁን።ወያኔን ማሶገድ እንጂ ለቀጣይነት በጥገና ለውጥ ወይም በስልጣን ክፍፍልማደስ የተቃዋሚነት ሳይሆን ያጋርነት ሚና ነው።

9. የኪነት፣የእስፖርት፣የስነጽሁፍ ባለሞያዎች ሆይ፤ ኢትዮጵያዊነት የተገነባው በፖለቲከኞች ብቻ አይደለም። መሰንቆና በገና፣ክራርና ዋሽንት ይዘው ጦር ሜዳ ዘምተው ሰራዊቱን፣ በቀረርቶና ፉከራ እያነቃቁና እያደፋፈሩ በግንባር በተሰለፉ ድምጻውያን፣ ምሁሮች በብዕራቸው በብራና ላይ ጽፈው፣በነደፉት ሥዕላቸው፣በጥልፋቸው፣ታሪካችንን፣ባህላችንን፣ እምነታችንን አንጸባርቀው፣ ቋንቋችንን በፊደላት ቀምረው፣ለአንድነታችን ምልክት የሆነውን የነጻነታችንን አርማ ፣ አረንጓዴ፣ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ቅርጽ አሲዘው ያወረሱን በጎሳ ያልተከፋፈሉት ድንቆቹ አያት ቅድመአያቶቻችን፣ እናቶቻችንና አባቶቻችን ናቸው።የነሱን አርማ መከተልና ማስከበር የማንኛውም ትውልድ አላፊነት ነው።በመሆኑም ይህንን የጋራ እሴቶቻችንን ለማጥፋት ተልእኮ ይዞ ላለፉት 27 ዓመታት በማተራመስ ላይ ያለውን የወያኔንና ግብረአበሮቹን ከይሲ ተግባር ማጨናገፍ የእናንተም ግዴታ መሆኑን እወቁ።በመድረክ ወይም በገበያ ላይ የምታግበሰብሱት ዋጋቢስ ብር አይማርካችሁ።ትልቁ ሃብት ማለት መብት የተከበረበት የትልቅ አገር ባለቤት መሆን ነው።ለዚያ ለሚያበቃችሁ ትግል ተሰለፉ።ነገ የሃፍረት ማቅ ከመከናነብ ይልቅ በሚያስከብረውና በሚያኮራው አገር ወዳድነት መግለጫ በሆነችው በጥንቷ ሰንደቅ ዓላማ ስር ተሰለፉ።

*የኢትዮጵያሕብረት፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ የህዝቧ ጽኑ አንድነት፣ እኩልነትና የህግ የበላይነት የሚከበርበት ፍትህዓዊ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመመሥረት በግንባር ቀደምትነት ለማስተባበር በክፍለሀገር ማህበራት የተመሰረተ ብሄራዊ ድርጅት ነው*

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!

የኢትዮጵያ ሕብረት

1/05/2018